# በምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት ቢሮ ስር ለ2007 ዓ.ም. በአራተኛው ሩብ አመት የተከናወኑ ተግባራትና ጥቅል የአመቱ የስራ ክንውን ሪፖርት

## ክፍል ፲፡ ገለፃ

### 1. መግቢያ

ዩኒቨርሲቲያችን በሀገሪቱ ውስጥ ካሉትአንጋፋ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል ቀደምት ነው፡፡ ላለፉት 60 ዓመታት በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራትና ሀገራዊ ጠቀሜታ ያስገኙ ዘርፈ-ብዙ የምርምር ውጤቶችንበማፍለቅና መልካም ተመክሮዎችንበማስፋፋት ሲሰራ ቆይቷል፡፡

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ጉዳዮች ቢሮየዩኒቨርሲቲዉን የምርምርና የምርምር ውጤቶች ስርጸትን በማስተባበርና በመከታተል ዩኒቨርሲቲው በምርምር ስራና ውጤት የላቀ ደረጃ እንዲደርስ ያላሰለሰ ጥረት በማደረግ ላይ ይገኛል፡፡ ቢሮው በርካታ የምርምር ውጤቶችንና ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅና በማሰራጨት የማህበረሰቡ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት የበኩሉን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት ዩኒቨርሲቲው ወደ 150 የሰብል ዝርየዎችንና ሌሎች በርካታ ቴክኖሎጂዎችን አመንጭቶ በጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በርካታ ሳይንሳዊ የምርምር ውጤቶችን በአገርአቀፍና በዓለም-አቀፍ ድርሳናትና መጽሀፍት መልክ አሳትሟል፡፡

ከ1980ዎቹ ጀምሮ ዩኒቨርሲቲው ከግብርና በተጨማሪ ሌሎች በርካታ የትምህርት መስኮች መከፈትን ተከትሎ የምርምርና ስርጸት ዘርፉም ያደገ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በ6 አንኳር የምርምር የትኩረት መስኮች ስራውን እያካሄደ ይገኛል፡፡ እነኚህ የምርምር ትኩረት መስኮች ዩኒቨርሲቲው በመማር-ማስተማርና ምርምር እንዲሁም በማህበረሰብ አገልግሎት ተሳትፎውን ለማላቅና ራዕዩን ለማሳካት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ቢሮው የተጠቀሱትን የትኩረት መስኮች ለማሳካት በምርምር ቡድኖችና አጋርነት፤ በምርምር ስርጸትና ህትመት፤ እና በምርምር ፋሲሊቲዎች ዳይሬክቶሬቶች ተዋቅሮ እየሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የየትኩረት መስኮቹን መሪዎች ለመመደብ በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡

በዚህም መሰረት የምርምር ቡድኖችና አጋርነት ዳይሬክቶሬት የምርምር ስራዎችን የማስተባበር፤ የመከታተል፤ ድጋፍ የመስጠት ስራና የዩኒቨርሲቲውን የምርምር ስራ ከሌሎች ባለድርሻ አካላትና የምርምር ሀገር ዓቀፍና አለም ዓቀፍ ድጋፍ አድራጊ ድርጅቶች ጋር የማስተሳተር ስራዎችን ያከናውናል፤ የምርምር ስርጸትና ህትመት ዳይሬክቶሬት የምርምር ውጤቶችን፣ እውቀቶችን፣ ቴክኖሎጂዎችንና መልካም አሰራሮችን ለተጠቃሚው ማድረስ፣

እነዲደርሱ ማድረግ እና የዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎችና የድህረ-ምረቃ ተማሪዎች የምርምር ግኝቶች በምርምር ድርሳናት፣ በመጻጎፍትና በመጽሃፍ መልክ፤ በፕሮሲዲንግ እና በሌሎች የህትመት አይነቶች እንዲታተሙ የማበረታታት፤ የማሳተምና የማስራጨት ስራዎችን ያከናውናል፤የምርምር ፋሲሊቲዎች ዳይሬክቶሬት የምርምር ፋሲሊቲዎችን የማስተዳደር፤ የማስፋፋት፤ የማዘመንና በአግባቡ እና በፍትሃዊነትስራ ላይ እንዲውሉ የማድረግ፤ የምርምር ግብዓቶችን የመለየት፣ የማቅረብ፣ የማከፋፈል፣ በተገቢው መንገድ ስራ ላይ መዋላቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

## 2. የምርምር ጉዳዮች ቢሮ ተልዕኮ፣ ራዕይ፣ እሴትና መሪ ቃል

### ተልዕኮ

ፍላጉት-ተኮርና ጠቃሚ ምርምሮችን በተለያዩ መስኮች በማካሄድ የምርምር ቴክኖሎጂዎችን፣ እውቀቶችንና መልካም ተመክሮዎችን በማፍለቅ፣ በመለየትና በማስራጨት የህብረተሰቡን ኑሮ ማሻሻልና ማሳደግ፡፡

### ራዕይ

**የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ በ2025 G.C ከአፍሪካ በምርምር ተመራጭ ከሆኑ ጥቂት ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አነዱ እነዲሆን ማስቻል፡፡**

### እሴት

1. **አካዳሚያዊ ነፃነት፡**የመማር-ማስተማርና የምርምር ስራዎች በነጻነትና በዲሞክራሲያዊ መንገድ እንዲካሄዱ፣ ግለሰቦች ጥልቅ ምርምር ማድረግ እንዲችሉ፣ በመማር-ማስተማር፣ በምርምርና በልማት ስራዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ዩኒቨርሲቲው በቁረጠኝነት ይሰራል፡፡
2. **ቁርጠኝነት፡** የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የተሰጣቸውን ስራና የተጣለባቸውን ሀላፊነት ዕውቀታቸው በፈቀደ ደረጃ በቁርጠኝነት፣ በተነሳሽነትና በታማኝነት ለመወጣት የሰራሉ፡፡
3. **መልካም አስተዳደር፡**ዩኒቨርሲቲው ዴሞኪራሲያዊ፤ ግልፅ፤ ሁሉን አሳታፊ፤ ሀላፊነትና ተጠያቂነት የተመላበት አመራርንያሰፍናል፤የእኩል ተጠቃሚነት መርሆን ያራምዳል፡፡
4. **ልዩነትን ማክበር፡**ዩኒቨርሲቲው እኩልነትና ፍትሀዊነት በሁሉም መልኩ እነዲሰፍን ልዩነቶችን (በፆታ፤በብሄር፤በሀይማኖት፤በዘር፣ በጎሳ፤ በእድሜ፤ በኣካል ሁኔታ፤ ወዘተ..) አክብሮ ይሰራል፡፡

5. **ሙያዊ አሰራርን መሰረት ማድረግ፡-** የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ለላቀ ሁሉን ዓቀፍ ሙያዊ ስነምግባር ተገዥ ይሆናል፡፡
6. **በጋራ የመስራት ባህልንማዳበር፡-**የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እርስ በርስና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመግባባት በጋራ የመስራት ባህልን ያዳብራሉ፤ የእኛነትን መንፈስና ሃላፊነትን የመቀበል መርሆ ያሳድጋሉ፡፡
7. **የፈጠራ/ግኝት ክህሎትን ማዳበር**፡-የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብየስራ፣ የአዳዲስ ግኝቶችና ፈጠራዎች ባለቤት የመሆንና አቀናጅቶ የመተግበር ባህልን ያዳብራል፡፡
8. **ተፈጥሮና አካባቢን መንከባከብ፡-**ዩኒቨርሲቲው የተፈጥሮ ሀብትንና አከባቢን ለመጠበቅ፣ለመንከባከብና፣ በአግባቡና ተፈጠሮን በማይጎዳ መልኩ ለመጠቀም በቁርጠኝነት ይሰራል፡፡

## መሪ ቃል

ለልማት መሰረት እንጥላለን!

## 3. ከዩኒቨርሲቲው ወደ ምርምር ጉዳዮች ቢሮ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች፣ ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤትና ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈጸሙ ዋናዋና ተግባራት በትኩረት መስክ

# የትኩረት መስክ 2፡ በምርምር መላቅ

**ግብ 1.** ፍላጎት ተኮር የምርምር ፕሮግራሞችን፣ ተግባራትን፣ ውጤቶችን እና አገልግሎቶችን ማሳደግ

**ውጤት 1፡**የጨመረ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ቴክኖሎጂዎችና አገልግሎቶችእና ያደገ የደንበኞች እርካታ

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. በዩኒቨርሲቲው የገንዘብ ድጋፍ በመካሄድ ላይ ያሉ የምርምር ስራዎችን ሪፖርት (ሳይንሳዊ ውጤቱን) ማቅረብ (የ2005 ዓ.ም ድጋፍ)

   በመንግስት በጀት በ2005 አመተ ምህረት የተጀመሩ እና በ 2006 የበጀት አመት የተጠናቀቁ 36 የምርምር ስራዎች በግብርና፤ በትምህርት፤ በህብረተሰብ አኗኗር፤ በጤና፤ በኢኮኖሚ እና በሌሎች የምርምር ዘርፎች የተሰሩ ሲሆን፤ ሪፓርታቸው ተጠናቆ ገብቶ በአብዛኛው በዘንድሮው የምርምር ጉባኤ ላይ ቀርበዋል፡፡

2. በዩኒቨርሲቲው የገንዘብ ድጋፍ በመካሄድ ላይ ያሉ የምርምር ስራዎችን ማጠናቀቅ (የ2006 ዓ.ም ድጋፍ)

በመንግስት በጀት በ 2006 አ.ም የተጀመሩ 44 የምርምር ስራዎች በግብርና፤ በትምህርት፤ በህብረተሰብ አኗኗር፤ በጤና፤ በኢኮኖሚ እና በሌሎች የምርምር ዘርፎች በሂደት ላይ ያሉ ሲሆን ስራቸውንም ሙሉ በሙሉ በ 2007ዓ..ም የሚጠናቀቁ ናቸው፡፡ ከተፈቀዱት 44 የምርምር ስራዎች ውስጥ 15 ያህሉ ምርምራቸውን የጨረሱ በመሆኑ የማጠቃለያ ሪፓርት አስገብተዋል፡፡

3. በሲዳ (SIDA) የገንዘብ ድጋፍ በግብርና ሳይንስ መስክ በመካሄድ ላይ ያሉ የምርምር ስራዎችን ሪፖርት (ሳይንሳዊ ውጤቱን) ማቅረብ (የ2005 ዓ.ም ድጋፍ)

በሲዳ (SIDA) የገንዘብ ድጋፍ በግብርና ሳይንስ መስክ በመካሄድ ላይ የነበሩ የምርምር ስራዎች ሪፖርት ከሞላ ጉደል ተጠናቆ ገብቶአል፡፡

4. ለ2007 ዓ.ም. በጀት ለውድድር የሚቀርቡ የምርምር ንድፈ ሃሣቦችን መጋበዝና በግልጽ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ የንድፈ ሃሣቦችን መረጣ ማካሄድና የምርምር ገንዘብ ድጋፍ ሰጥቶ ስራን ማስጀመር

በመንግስት በጀት በ 2007 አ.ም ለሚጀምሩ አዳዲስ የምርምር ስራዎች ተመራማሪዎች የምርምር ንድፈ ሀሳባቸውን እንዲያስገቡ ጥሪ የተደረገ ሲሆን፡ ጥሪውም አዲስ በጸደቀው የምርምር የትኩረት አቅጣጫ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት 270 ያህል የምርምር ንድፈ ሀሳቦች በስድስቱ የምርምር የትኩረት አቅጣጫ አመልክተዋል፡፡ እነዚህም የምርምር ንድፈ ሀሳቦች የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ግምገማ ተደርጎባቸው 107 ለምርምር ድጋፍ ተመርጠው ስራቸውን ጀምረዋል፡፡

5. ለ2007 ዓ.ም ለውድድር ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ያለፉ የምርምር ንድፈ ሃሣቦች የሚቀርቡበት መደረክ ተዘጋጅቶ የምርምር ንድፈ ሃሳብ መረጣ ተካሂዷል፡፡
6. በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲቱዩት የገንዘብ ድጋፍ በግብርና ሳይንስ መስክ ምርምር ለማካሄድ በታቀደው መሰረት 128 የምርምር ስራዎች በተለያዩ የምርምር መስኮች እየተከናወኑ ናቸው፡፡

7. የተለያዩ የምርምር ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የምርምር ድጋፍ ማስገኘት

የተለያዩ የምርምር ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የምርምር ድጋፍ ማስገኘት ረገድ በርካታ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ለድጋፍ ለተለያዩ ድርጅቶች የተላኩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ሁለት ፕሮጀክቶች ማሸነፋቸው ተረጋግጧል፡፡

8. ለዝርያ ልቀት ደርሰው በሂደት ላይ የሚገኙትን የምርምር ስራዎች ማጠናቀቅና ለብሄራዊ ዘር አጽዳቂ ኮሚቴ ማቅረብ፡
ለዝርያ ልቀት የደረሱ የተለያዩ የምርምር ውጤቶች ለብሄራዊ ዘር አጽዳቂ ኮሚቴ የቀረቡ ሲሆን፤ ከነዚህም እንድ **የማሽላ ዝርያ ተቀባይነት አግኝቶ ዝርያው ዩኒቨርስቲው ስም ተመዝግቦ ተለቋል**፡፡

9. በምስራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ አሁን በዩኒቨርሲቲው የተሠራጩ ቴክኖሎጅዎችን ቅቡልነት፣ ያሉበትን ደረጃ እና ተግዳሮቶችን መዳሰስ

በምስራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ አሁን በዩኒቨርሲቲው የተሠራጩ ቴክኖሎጅዎችን ቅቡልነት፣ ያሉበትን ደረጃ እና ተግዳሮቶችን ለመዳሰስ በተደረገው ትረት፣ የስራ ቦታ መረጣ፣ የመጠይቆች ዝግጅትና ፍተሻ፣ እና ተያያዥ ጉዳዩች ተከናውነው በተሽከርካሪ እጥረት ምክንያት የስራውን ወሳኝ ስራ ማለትመ (መረጃ መሰብሰብ) ማከናወን አልተቻለም፡፡ በቀጣዩ ሩብ አመት ለማከናወን ጥረት ይደረጋል፡፡

10. በምስራቅ ኢትዮጵያ በአራት ወረዳዎች ውስጥ  የስንዴ ቴክኖሎጂ ቅቡልነት ላይ  የዳሳሳ ጥናት ማካሔድ

በምስራቅ ኢትዮጵያ በአራት ወረዳዎች ውስጥ  የስንዴ ቴክኖሎጂ ቅቡልነት ላይ  የዳሳሳ ጥናት ለማካሔድ የታቀደ ቢሆንም ከተባባሪ አካላት በወቅቱ በጀት ባለመላኩ ስራውን ማካሄድ አልተቻለም፡፡

11. ሁለት በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኮሩ ማለትም በ Investigating Community-Based Conflict Dynamics in Selected Woredas of East Hararghe Zone ርዕስ ላይ በድምሩ 40 ተሳታፊዎች የተገኙበት እና Energy, Environment, and Development በሚል ርዕስ በተዘጋጀ ዓውደ ጥናት ላይ 155 ተሳታፊዎች የተገኙበት ኮንፈርነሶችን ተካሂደዋል፡፡

12. ለ2008 ዓ.ም. በጀት ለውድድር የሚቀርቡ የምርምር ንድፈ ሃሣቦችን ለውድድር መጋበዝ

ለ2008 ዓ.ም. በጀት ለውድድር የሚቀርቡ የምርምር ንድፈ ሃሣቦችን ለውድድር የተጋበዘ ሲሆን 341 የምርምር ንድፈ ሀሳቦች ለምርምር ጽ/ቤት ገብተዋል፡፡

13. ለ2008 ዓ.ም. በጀት ለውድድር ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ያለፉ የምርምር ንድፈ ሃሣቦችን የሚቀርቡበት መድረክ ማዘጋጀት፡

ለምርምር ጽ/ቤት ከገቡት 341 የምርመር ንድፈ ሀሳቦች ውስት 240 የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ያለፈ ሲሆን፣ እነዚሁ ንድፈ ሀሳቦች በስድት ትይዩ መድረኮች የቀረቡ ሲሆን፣ በዩኒቨርስቲው በሚገኙ ልምድ ባካበቱ ተመራማሪዎች ግምገማ እና አስተያየት የተሰቸው ሲሆን በውጤታቸው ቅደም ተከተል መሰረት ተቀምጠዋል፡፡ በመሆኑም በአዲሱ በጀት አመት ከበጀቱ ጋር በማነጻጸር የበጀት ድጋፍ የሚሰጣቸው የምርመር ንድፈ ሀሳቦች የሚለዩ ይሆናል፡፡

14. 32ኛ አመታዊ የምርምር እና ስርፀት  ጉባኤ በስድስቱ የምርምር የትኩረት አቅጣጫዎች ማካሔድ

32ኛ አመታዊ የምርምር እና ስርፀት ጉባኤ በስድስቱ የምርምር የትኩረት አቅጣጫዎች ለማካሔድ በተያዘው እቅድ መሰረት በሶስት የተለያዩ ክፍሎች በአንድ ግዜ ለሶስት ቀናት የተካሄደ ሲሆን በዚሁ ጉባኤ ላይ ከተላያዩ መንጋስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አጋር ድርጅቶች የተወከሉ ወደ 250 የሚደርሱ ተሳታፊዎች ተገኝተው ወደ 80 የምርምር ስራዎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡










15. **በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኮሩ ኮንፈረንሶች ላይ በኮሌጆች ጥያቄ መሰረት ማካሄድ**

በዚህ አመት አመት የተለያዩ አምስት አገር አቀፍ ኮንፈረንሶች የተካሄዱ ሲሆን፤ በአራተኛው ሩብ አመት ውስጥ ሶስት ተካሂዷል። እነዚህም አንደኛው በአዋሽ ተፋሰስ የመልሶ ማልማት ፕሮጀክት ቀረጻ ሲሆን፤ የግብርና ኮሌጅ፤ የቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ከዩኒቨርስቲው ሲያስተባብሩት፤ ከውጭ ደግሞ የሽለቆዎች ልማት ድርጅትና ሌሎች ድርጅቶች ተሳትፈውበታል። ሁለተኛው ደግሞ የመስራቅና ምእራብ ሐረርጌ ዞኖችን ያካተተው የሰላምና ልማት ጉባዔ፤ ከመሬት ጋር ተያያዥነት ያለቸውን ግጭቶች ለማስወገድ ታሳቢ ተደርጎ የተካሄደ ጉባኤ ነው።

16.የተሸሻሉ የስኳር ድንች ዘር ችግኝ (ቁርጥራጭ) ስርጭት ስራ ማከናወን

በሃምሌ ወር በተከሰተው የዝናብ እጥረት ምክንያት በማሳቸው ላይ ሰብላቸው ለጠፋባቸው አርሶአደሮች በ FAO ፕሮጀክት ለአፋር ክልል እንዲሁም ለድሬደዋ መስተዳድር ብዛቱ 1,675,000 የሚሆን አዱ የተባለ የስኳር ድንች ዝርያ ቁርጥራጮች (ችግኞች) ለ1675 ገበሬዎች ተሰረጭቷል።

17.በህብረተሰብ ተሳትፎ በተፋሰስ ላይ የተሠሩ የዓፈርና የዉሃ ዕቀባ ስትራክቸሮች ላይ የዛፍ ችግኞችን መትከል

በሜታና በሀብሮ ወረዳዎች በተመረጡ ሁለት ተፋሰሶች ላይ በ 2006 ዓ.ም. የክረምት ወራት በህብረተሰብ ተሳትፎ የተለያዩ የዛፍ ችግኞች ተተክሏል። ችግኞቹ የለሙት ከየወረዳዎቹ የግብረና ጽ/ቤቶች ጋር በመተባበር በዬወረዳዎቹ በሚገኙ ችግኝ ጣቢያዎች ሲሆን ይህም የአከባቢዉን ሥነ-ምህዳር በቅድሚያ የተላመዱ ችግኞችን ለአካባቢዎቹ ለማድረስ አስችሏል። በዚህም ስራ በሁለቱ ወረዳዎች ከ18000 (አስራስምንት ሺ) በላይ የተለያዩ የዛፍ ችግኞች ለመትክል ተችሎል።




18.የፍራፍሬና ዘርፈ-ብዙ (Multi-purpose) ጥቅም ያላቸውን የዛፍ ዝሪያዎችን በመኖሪያ አካባቢና በእርሻ ቦታዎች ማስተከል

አረሶ አደሮች የፍራፍሬና ዘረፈ-ብዙ ጥቅም ያላቸዉን የዛፍ ዝሪያዎችን በመትከል ከዛፎቹ ከሚያገኙት ጥቅም ጎን ለጎን አከባብያቸዉንም እንዲንከባከቡ ለማስቻል ታስቦ በተከናወነዉ ስራ በሀብሮ ወረዳ 20 አርሶአደሮች፣ በኮምቦልቻ ወረዳ 45 አርሶአደሮች፣በሐረማያ ወረዳ 30 አረሶአደሮች በድምሩ 95 (ዘጠና አምስት) አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ እያንዳንዱ ተሳታፊ አርሶአደር በነፈስ ወከፍ 20 (ሀያ) የዛፍ ችግኞችን በማሳዉ ዙሪያና በመኖሪያቸዉ አከባቢ እንዲተክል ተደርጓል፡፡

19.የ2012/13 (30ኛ) የምርምርና ስርፀት ኘሮሲዲንግ ህትመት በ500 ቅጂ ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል፤፤

20.የBiodiversity Workshop ፕሮሲዲንግን ለማሳተም ኮሚቴ ተዋቅሮ የመጀመሪያ ዶክመንት (first draft) የተዘጋጀ ቢሆንም ተጨማሪ ማስተካከያ (further edition) በማስፈለጉ ተጨማሪ ጊዜ ጠይቋል።

21. የተሻሻሉ የቲማቲም፤ የበቆሎ፤ የስንዴ፤የባቄላ፤ የስኳር ድንች አመራረት  እንዲሁም የሰብሎችን የአጣምሮ መዝራት ኤክስቴንሽን መመሪያዎችን (Manuals) ማዘጋጀት

የተሻሻሉ የቲማቲም፤ የበቆሎ፤ የስንዴ፤የባቄላ፤ የስኳር ድንች አመራረት  እንዲሁም የሰብሎችን የአጣምሮ መዝራት ኤክስቴንሽን መመሪያዎችን (Manuals) የተጋጁ ቢሆነም የመመሪያዎቹ የመጀመሪያ ደረጃ ጽሁፍ ተጠናቆ በቋንቋ እርማትና ማስተካከያ እንዲሁም ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች የመተርጎም ስራ እየተሰራ ነው፡፡

22.በተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ፤ በእንስሳት ሳይንስ በዕጽዋት ሳይንስ አንዲሁም በግብርና ምጣኔ ሀብት የትምህርት መስኮች የማስተርስ መመረቂያ ድርሳናትን አብስትራክት 4 ጥራዝ በሙያ መስክ ለማሳተም በተያዘው እቅድ መሰረት ታትሞ ተሰራጭቶአል፡፡

23.የተሻሻሉ የበቆሎና የድንች ቴክኖሎጅዎችን  የፓይለት ማስፋፋት (Pilot-scaling) ስራ መስራት

የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን የማስፋፋት ስልት ከመቀየስ አንጻር መልካም ተሞክሮ ለማግኘትና ልምድን ለመቀመር ይቻል ዘንድ በ2006/7 የምርት ዘመን በተመረጡ ሁለት የምርት ቴክኖሎጂዎች ላይ የማስፋፋት ፓይለት ሥራ ተካሂዷል፤፤ የተሻሻሉ የድንች እና የድቃይ በቆሎ አመራረት ተክኖሎጂዎች ለማስፋፋት (ፓይለት) የተመረጡ ቴክኖሎጂዎች ሲሆኑ፤ የድንች ቴክኖሎጂ በሐረማያ፣በኮመቦልቻ እና በግራዋ ወረዳዎች በድምሩ 113 አርሶደሮች ላይ የተሰራጨ ሲሆን የድቃይ በቆሎ ቴክኖሎጂ ደግሞ በሀብሮ ወረዳ በድምሩ ለ130 አርሶአደሮች እንዲደረስ ተደርጓል፡፡







24. የተለያዩ ሳይንሳዊ የምርምር መጣጥፎችን  (articles) በሚገመገሙ (Peer-reviewed) ጆርናሎች እንዲታተሙ  የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ

የተለያዩ ሳይንሳዊ የምርምር መጣጥፎችን (articles) በሚገመገሙ (Peer-reviewed) ጆርናሎች እንዲታተሙ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ በተያዘው እቅድ መሰረት የጥራት መስፈርት ያሙሉትና ድጋፍ የተደረገላቸው አምስት መጣጥፎች ናቸው፡፡

25. የምርምር ፖሊሲና መመሪያ ሰነድ ለማዘጋጀት በተያዘው ዕቅድ መሰረት ረቂቁ ተዘጋጅቶ ሰነዱን ለማዳበር ውይይት እየተደረገበት ይገኛል።
26. የEast African Journal of Sciences 6ኛ (2012)እትም ቁጥር ሁለት በ500 ቅጂ ታትሞ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል፡፡
27. የEast African Journal of Sciences 7ኛ (2013)እትም ቁጥር አንድተዘጋጅቶ ታትሞ ለስርጭት ተዘጋጅቶአል፡፡ ህትመቱም በድረ ገጽ ተለቋል፡፡
28. የEast African Journal of Sciences 8ኛ (2014) እትም ቁጥር አንድ ለህትመት የተዘጋጀ ሲሆን ህትመቱም በድረ ገጽ ተለቋል፡፡ የዚሁ እትም ቁጥር ሁለት ደግሞ የመጨረሻው የዝግጅት ስራ ላይ ነው፡፡
29. የEast African Journal of Sciences ድረ ገጽ (online submission and review) ማዘጋጀትና ስራ ማስጀመር

    የ East African Journal of Sciences ድረ ገጽ (online submission and review) ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ መጣጥፎችና ድርሳናት ለአንባቢያን በቀጥታ ማንበብና ማውረድ እንዲችሉ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የመጣጥፍ ደራሲያንና ገምጋሚዎች ስራዎቻቸን በቀጥታ ማውረድና መጫን እንዲችሉ ተደርጓል፡፡ይህም የጆርናሉን ዓለማቀፋዊ ተደራሽነት ያሰፋዋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

30. በ East African Journal of Sciences እንዲታተሙ የሚቀርቡ ሳይንሳዊ መጣጥፎችን (Manuscripts) በባለሙያዎች ማስገምገም
    በአመቱ ወደ 120 የሚሆኑ መጣጥፎች በተለያዩ ገምጋሚዎች ተገምግመው በውጤታቸው መሰረት ተቀባይነት ያገኙት እንዲታተሙ፣ ተቀባይነት ያላገኙት ውጤታቸው ተመራማሪዎቹ እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

31. የህትመት መገምገሚያ መመሪያ ማዘጋጀት
    የምርምር መጽኄት ላይ የሚወጡ የምርምር ውጤት ጽሁፎችን ደረጃ ለመገምገምና ወደፊት ሊወጡ የሚችሉ የምርመር ጽሁፎችን ጥራት ለማሻሻል ታስቦ መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ይኸው መመሪያ ለውይይት ቀርቦ አስፈላጊው ማሻሻያ እንዲደረግበት ግብረ መልስ ተወስዶአል። ይኸው የማሻሻያ ስራ እየተሰራ ሲሆን በቅርቡም ተስተካክሎ ለሴኔት ይቀርባል።

32. የዩኒቨርሲቲውን የምርምር የትኩረት መስኮችን ሰነድ ማሳተም

    የዩኒቨርሲቲው የምርምር የትኩረት መስክ ሰነድ ስምንት (8) ምዕረፍ እና 160 ገጽ የያዘ 500 ቅጂ ታትሞ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡

33. በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል ከተመራማሪዎች በቀረበየምርምር እይታና የማህበረሰቡን ፍላጎት ባማከለ ሁኔታ ምርምር እያካሄደ 8ሣይንሳዊ ጽሁፎችንና ችግር ፈቺ ቴክኖሎጅዎችን ማቅረብ ተችሏል።
34. በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል በሚሰሩ የምርምር ማእከል ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሁለት ግዜ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የተሰራ ሲሆን፣ ወደፊትም ከነዚሁ አካላት ጋር በምን መስክ አብረን ልንሰራ እንደምንችል አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል፡፡
35. በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል የሚወጣ ኒውስሌተር (Newsletter) ለማዘጋጀት በተያዘው እቅድ መሰረት፣ የመጀመሪያው ኒሰውስ ሌተር ተዘጋጅቶአል፡፡

36. በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል በሚሰሩ የምርምረ ስራዎችን በመጠቀም የፖሊሲ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ሀሳቦች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነኚህም የመነሻ ሀሳቦች ከሚመለከታቸው የጤና አካላት ጋር ለመወያየት በሂደት ላይ ነው፡፡

37. ነባር ኢንስቲቲዩቶችን መልሶ የማዋቀርና ስራ የማስጀመር እንዲሁም አዲሶችን ለማቋቋም የሚረዳ መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ በ ጽ/ቤት ደረጃ ውይይት እየተካሄደበት ሲሆን በቀጣይም በዩኒቨርሲቲ ዓቀፍ ደረጃ ለውይይትለማቅረብ ታቅዷል።

38. ለተለያዩ የሰብል ዝርያዎቸ የዘር ገበያ መለየትና የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ
ለተለያዩ የሰብል ዝርያዎቸ የዘር ገበያ መለየትና የአዋጭነት ጥናት ተካሂዶ የጥናቱ ውጤት በተለያዩ አውደ ጥናቶች ላይ ቀርቧል፡፡

39. የገበያ ትስስርን ለመፍጠርና  የዘር ግብይትን ለማሳለጥ ሁለት አጋሮችን ማለትም CARE-Ethiopia ና FAO ተለይተዋል።

40. የተለያዩ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ስጪ ተቋማትን መለየትና ከዘር አምራች ማህበራት ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ እነዚሁ አካላትና ከ10 ዩኒየን የተውጣጡ አባላት የተሳተፉበተ አውደ ጥናት ተካሂዶ በትብብር መስራት በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ውይይት ተካሂዷል።ከዚሁ ጋር ተያይዞ እግዝቢሽን ተካሂዷል።

41. የንብ እርባታ የአርሶአደሮች የምርምር ቡድን ተቋቁሟል፡፡

42. የተሸሻሉ የዶሮ ዝርያዎችን ለተመረጡ ሴት አርሶ አደሮች ማሰራጨት

የተሻሻሉ የዶሮ ዝርያዎችንና የአረባብ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ሴት አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ለማድረግ ተስቦ በመካሄድ ላይ ያለ እንቅስቀሴ ሲሆን በሜታ ወረዳ ለተመረጡ 40 (አርባ) ሴቶች ለያንዳንዳቸዉ15 (አስራ አምስት) በድምሩ 600 (ስድስት መቶ) ቦቫን ብራዎን የተባሉ የዕንቁላል ጣይ የዶሮ ዝርያዎች ተሰራጭቷል፡፡



43. የመልካም ተመክሮና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማላመድ ማስተዋዋቅና ማስፋፋት

በዚህ ዓመት በ6 የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከል ላይ 23 ቴክኖሎጂዎችን ማላመድና ማስተዋወቅ ስራ ለመስራት ታቅዶ በዚሁ መሰረት በጭናክሰን፣ በሀረማያ፣ በቀርሳ፣ በጎሮ-ጉቱ፣ በድሬ-ጥያራ፣ ወረዳዎች ና በድሬዳዋ አዋሌ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከላት 19 የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን የማላመድ ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ ቴክኖሎጂዎቹም 6 የበቆሎ ዝሪያዎች (BH661,Gibe-2,Malkasa-4, Gibe-composite, Rare-I, Jibat, & PHQP-545) ፤ አራት የማሽላ ዝሪዎች( ሙይራ-1! ሙይራ-2 ተሻለ እና ሆርማት)፤ 2 የድንች ዝሪያዎች (ቡቡና ጉዳኔ)፣ሦስት የስንዴ ዝሪዎች (ዲገሉ፣ ቀቀባ፣ እና ዳንዳኣ)፣ 3 የደጋ ጥራጥሬ ምርጥ ዘሮች (ባቄላ፣ አተር እና ሽምቡራ) እና 3 የለውዝ ዝሪያዎችን (ባሃ-ጉደ፣ ባሃ-ጂዱ እና ሰዲ) ናቸው ፡፤

44. የተሸሻሉ የሰብል ዘሮች ብዜት ስራ ማከሂድ

በተሸሻሉ የሰብል ዘሮችን በ8.5 ሄክታር መሬት ላይ ለማባዛት ታቅዶ የተከናወነው 28.7 ሄክታር መሬት በ መስራች ምርጥ ዘር እንዲሸፈን ተደርጓል፡፡

በቀጣይ ሩብ አመታት የተለያዩ ዘሮችን ለማሰራጨት ይረዳ ዘንድ በዚህኛው ሩብ አመት በምርምር ጣቢያዎች ላይ 612 ኩንታል የተለያዩ የድንች! የስንዴና የማሽላ መስራች ዘሮችተባዝተዋል።

ሠንጠራዥ1፡ በምርምር ጣቢያዎች ላይ የተዘሩ የተሸሻሉ የተሳያዩ የሰብል ዘሮችና የተሸፈነው የመሬትመጠን የተገኘው የምርት መጠን፡-

| ተ.ቁ | ምርምር ጣቢያ ስም | የተሸሻሉ የሰብል ዘር ዓይነት | ዝሪያ | የተዘረው የዘር መጠን (ኩ/ል) | የተሸሻፈና መሬት መጠን(ሄክታር) | የተገኘው ጠቅላላ ምርት (ኩ/ል) | የተገኘው ምርት በሄ/ር (ኩ/ል) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሐረማያ ዩንቨረሲቲ ዋና ግቢ | ድንች | ጉዳኔ | 40 | 1.7 | 564.0 | 331.8 |
| 2 | ፊድስ ምርምር ጣቢያ | ስንዴ | ቀቀበ | 1.40 | 0.74 | 18.0 | 24.32 |
| | | ማሽላ | ተሻለ | 0.13 | | 5.5 | |
| | | | ሆርማት | 0.05 | | 0.5 | |
| | | ቦሴቄ | ፊዲስ | | | 0.5 | |
| 3 | ሒርና ምርምር ጣቢያ | ስንዴ | ቀቀበ | 1.0 | 0.44 | 10.0 | 22.72 |
| 4 | ባቢሌ ምርምር ጣቢያ | ስንዴ | ቀቀበ | 0.50 | 0.25 | 2.5 | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ማሽላ | ተሻሰ | .07 | 0.25 | 2.0 | |
| | | ማሽላ | ሆረማት | 0.5 | 0.75 | 9.5 | |
| | | | | | | 611.5 | |



45. የተሻሻሉ የሰብል ዘሮችን ለተጠቃሚዎቸ ማሰራጨት

በክረምት ዝናብ መዘግየት ምክንያት ሰብላቸው ለጠፋባቸው በጥኒቁ፣ በቱጂ-ገቢሳ፤ በሀሮ-አዲ፣ በባቱ፣ በዳሞታ ቀበሌ ማህበር ውስጥ ለሚኖሩ ቁጥራቸው ከ300 በላይ ለሆነ አርሶ አደሮች 44 (አርባ አራት) ኩንታል የተለያዩ ቶሎ ደራሽ የሰብል ዝርያ ምርጥ ዘሮችን ተሰጥቷል፡፡ በተጨ 28.8 ኩንታል የሚሆን ምርጥ ዘር ለ4 ዘር አምራች ማህበራት ተሰራጭቷል፡፡

በአራተኛው ሩብ ዓመት ደግሞ 675 ኩንታል ዘር የተሰራጨ ሲሆን፤ በአጠቃለይ በአመቱ 1214 ኩንታል የተለያየ ዘር በግራዋ፤ በሐረማያ፤ ኮምቦልቻ፤ በሜታ፤ በቀርሳ እና በሌሎችም ወረዳዎች ተሰራጭቶአል፡፡

46. ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት ቴክኖሎጂን መስራት

ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት ቴክኖሎጂን ማስተዋዋቅ ማስፋፋት፡ በአመቱ 50 ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት ለተለያዩ ተጠቃሚዎች ለማሰራጨት ታቅዶ 49 ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት ተችሏል፡፡

47. የተሻሻሉ የዶሮ  ዝሪያዎችን ማስተዋዋቅ

የተሸሻሉ የዶሮ ዝሪያዎችን ማስተዋዋቅ፡ በሁለት የገጠረ ቀበሌ ማህበራት ማለትም በቢፍቱ ገዳ እና ድሬ ጠያራ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከላት ውስጥ የተሸሻለ የዶሮ እርባታ ዘዴን ለማስተዋወቅ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ከቢፍቱ ገዳ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከል የተገኘውን እነቁላሎች ለአርሶ አደሩ በማከፋፈል እንዲያስፈለፍሉ የተደረገ ሲሆን በዚህ ሩብ አመት 16 ቄቦችና 6 አውራዎች ምርት ለመስጠት ደርሰዋል፡፡ በኣጠቃላይ በአመቱ 77 የተሸሻለ ዝርያ ዶሮዎችን ወደ ተጠቃሚ ለማድረስ ተችሎአል፡፡



*ዘመናዊ የዶሮ እርባታ በተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት በድሬ ጠያራ እና ቢፍቱ ገዳ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከል*

48. የተሸሻሉ የንብ ቀፎዎችንና የማነብ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋዋቅ

ይህንን ቴክኖሎጂ በማስተዋወቅ አርሶ አደሩን በተለያየ መልኩ ተጠቃሚ ማድረግ የሚቻል ሲሆን  በተለይ በአገራችን እየተሰራበት የሚገኘው የንብ ማናባት ስራ በጣም ኋላ ቀር በመሆኑ የማር ምርታችንም በአማካኝ በአመት ከ 5ኪ.ግ የማይበልጥ ነው፡፡ ከዚሁ ባህላዊ ቀፎ የሚገኘው ማር ከጥራት አንጻር ሲታይ ሰም፣ እጭ፣ የአበባ ዱቄትእና ማር በአንድ ላይ የሚቀረጥ በመሆኑ ጥራቱ ላይ አይነተኛ ችግር አለው፡፡ እንዲሁም በዋጋው ውድ የሆነውን ሰም ማጣራት ባለመቻሉ ምክንያት አገልግሎት ላይ ሳይውል ይቀራል፡፡ በመሆኑም እነኚህን ችግሮች በመቅረፍ ከዘርፉ የተሻለ ውጤት ለማስገኘት ዘመናዊ የንብ ማናባት ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅና ማስፋፋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ በ2007 ዓ.ም በቢፈቱ ገዳ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከል ውስጥ ዘመናዊ የንብ እርባታ ስራን ለአርሶ አደሩ ለማስተዋወቅና ለማሰተማሪያነት እንዲያገለግል ታስቦ ሶስት(3) ባህላዊ የንብ ቀፎዎችን ወደ ዘመናዊ የንብ ቀፎ  የመገልበጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአመቱ በሀያ የንብ ቀፎዎች ዘመናዊ የንብ ማናባት ዘዴ ለማስተዋወቅ ታቅዶ ለዚሁ ስራ የሚሆኑ ሙሉ የዘመናዊ ንብ ማናቢያ ትጥቆች፤ የመገልገያ ቁሳቁሶችና አስር የንብ መንጋ ተገዝቶ ወደ ዘመናዊ ቀፎ ለማሸጋጋር ተዘጋጅቶአል፡፡



*በሐረማያ ዋናው ግቢ በንብ እርባታ ማእከል ባህላዊ የንብ ቀፎ ወደ ዘመናዊ የንብ ቀፎ ሲገለበጥ*

49. የተሸሻሉ የፍየልና የበግ ዝሪያዎችን ማስተዋዋቅ

የአነስተኛ አመንዣኪ እንስሳት የስጋ ምርት ጥራትና ብዛት ለማሻሻል ከደቡብ አፍሪካ የመጡ የቦር ፍሎችን ከአካባቢ የተመረጡ እንስት ፍየሎች ጋር በማዳቀል በሐረሪ ክልል የድሬ ጠያራ እና ኤረር ወልዲያ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከላት ላይ ዝርያ የማስተዋወቅና ማዳቀል ስራ ተሰርቷል፡፡ በዚህም በ2006 ዓ.ም የተወሰዱ ለእያንዳንዱ አምስት አምስት የአካባቢ አናቲት ፍየሎችና ሁለት 50% የተዳቀሉ የአንድ አመት ወንድ (ኮርማ) ፍየሎች ሲሆኑ በአሁኑ ሰአት 10 ግልገሎች ተወልደው በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኮርማዎችን በመጠቀም በኤረር ወልዲያ ቀበሌ ለአስር የአካባቢው ህብረተሰብ የማስጠቃት አገልግሎት ተሰጥቷል፤፤በድምሩ 20 ፍየሎች ለአርሶአደሮች ተሰራጭቷል። በዚህም በ2006 ዓ.ም ለቴክኖሎጂ ማሰተዋወቅ ስራ የተወሰደውን ኮረማ በመጠቀም በዚህ ሩብ አመት 40 የአካባቢ ፍየሎችን በማስጠቃት ዝርያ የማሻሻል ስራ መስራት በመቻሉ ክንውኑን ከእቅድ በላይ ሊያደርገው ችሏል፡፡ በአመቱ በድምሩ 100 የተሸሻሉ የፍየል ዝርያዎች በሐረማያ ዙሪያ፤ በኤረር ወልዲያ እና በድሬ ጠያራ ተሰራጭተዋል፡፡




*የፍየሎች ዝርያ ማሻሻያ ስራ በድሬ ጠያራና ኤረር ወልዲያ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከል*




*ምስል 5 የተለያዩ የመኖ ልማት ስራዎች ከፍየል እርባታው ጋር በተያያዘ በኤረር ወለወዲያና ድሬ ጠያራ*

50. ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ የተሸሻሉ የተክል ዝሪያዎችን ማስተዋዋቅና ማስፋፋት

በሶስት የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከላት (ቢፍቱ ገዳ፣ ድሬ ጠያራ እና ጨናክሰን ዤግዤግ) ላይ የእንስሳት መኖ ማምርት ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ በሶስቱም ቦታዎች አልፋልፋ፤ ፒጀንፒ እና ካውፒ የሚባሉ የመኖ ዝርያዎች 10 በ 10 ሜትር በሆነ ቦታ ላይ የተዘሩ ሲሆን አልፋልፋው በግማሽ አበባ የእድገት ደረጃ ከመድረሱም በላይ በሶስቱም ቦታዎች በጥሩ ሁኔታ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ሩብ አመት በድሬ ዳዋ ምርምር መእከል ግማሽ ሄክተር ላይ የአልፋልፋ ዘር በመባዛት ላይ ነው፡፡



*በጭናክሰን ወርዳ ዡግዡግ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከል በመስክ ላይ ያሉ የአልፋልፋና ፒጀን ፒ የእንስሳት መኖ ልማት ስራዎች*

51. ስትራቴጂክ ምርምር የአዳቃይ ዘር ብዜት እና እደሳ ስራ ማከናወን (germplasm regeneration, maintenance and multiplication)

በዩኒቨርርሲቲው የተለቀቁ የሰብል ዝርያዎችና እነርሱ የተገኙባቸው ብዝሃ ህይወት ለማቆየትና ወደፊት አዳዲስ ዝርያዎችንም ለማወጣት በተለያዩ የሙከራ ማሳዎች ዘሮቹ ተዘርተው እንዲመረቱ ተደርጓል፡፡

52. የተሸሻሉ ጊደሮችን ለተመረጡ ሴት አርሶ አደሮች ማሰራጨት

የተሻሻሉ የወተት ከብቶችንና የአረባብ ተክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ ሴት አርሶ አደሮችን ይበልጥ ተጠቃሚነታቸዉን ለማረጋገጥ በፕሮጀክቱ በተያዘዉ አቅጣጫ መሠረት በሜታ ወረዳ ለተመረጡ 10 ሴት አረሶአደሮች 10 (አስር) የቦረና ጊደሮች ተሰራጭቷል፡፡ በተጨማሪም 15 የጀርሲ ድቃይ ጊደሮችበሃረማያናበኮምቦልቻወረዳዎች በተመሳሳይ ሁኔታተሰራጭቷል፡፡








**ግብ 2.** የምርምር አጋርነትንና ትስስርን ማሳደግ

**ውጤት 1፡**የጨመረ የአጋሮች ብዛት

## ዋና ዋና ተግባራት፡

1. ምርምር የሚሹችግሮችን በቀጣይነት ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መለየት፣ የምርምር ንድፈ-ሃሳብ መቅረጽ

   ምርምር የሚሹችግሮችን በቀጣይነት ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር በመለየት፣ የምርምር ንድፈ-ሃሳብ ለመቅረጽ በተደረገው ጥረት፤ በምስራቅና ምእራብ ሐረርጌ እምስት አርብቶ አደርና ከፊል አርብሮተ አደር ወረዳዎች የጋራ ጥናት ለማካሄድ ከኦሮሚያ የአርብቶ አደር ልማት ፕሮግራም ጋር በተደረገው ስምምነት ሰባት የዩኒቨርስቲው ተመራማሪዎች ስራ ጀምረዋል፡፡

2. የሴቶችን የልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማጎልበት

   በተለያዩ የምርምርና ስርጸት ስራዎች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎና ተጠቃሚነት የማሳደግ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለምሳሌ በገበሬዎች ቀን ላይ የሴቶች ተሳተፎ ጨምሯል፤ የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የተሻሻሉ የጊደርና የዶሮ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እነዲሆኑ ተደርጓል፡፡

3. ለወረዳ ሙያተኞች፣ ለልማት ሰራተኞች፣ ለአርሶ አደሮችና ሌሎች ባላድርሻ አካላት ስልጠና ለመስጠት በታቀደው መሰረት ለ 855 ሰልጣኞች በተለያዩ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣በዘረ አመራረትና አያያዘ፣ በማህበር አደረጃጀተ፣ በመስኖ ውሃ አጠቃቀምና በተለያዩ የምግብ አዘገጃጀት ለይ ስልጠናዎቸ ተሰጥቷል።

  



## Apiculture Technologies...



Theoretical training



Disease inspection



Crude honey purification



Bees wax purification



Wax moulding

## Nutrition…

### ➢ Tomato processing for preservation







Tomato puree and ketchup



Sliced and blanched Tomato

### ➢ Potato tuber processing



Potato drying



Products of Potato and other locally grown crops



Nourishment of Products of Potato and other locally grown crops







4. በ(LSB) ሞዴል የማስፋፋት ስራ ላይ ለሚሳተፉ አጋሮች በግምገማና ክትትል፣ ግብይት፣ አደረጃጀትና ተጨማሪ ዘር እሴት ላይ ለ70 ዘር አምራች አርሶአደሮች፣ የልማት ሰራተኞች፣ የወረዳ ሙያተኞችና ለሌሎች አካላት ስልጠና ተሰጥቷል።

5. ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትና የሚመካከሩበት የውይይት መደረክና ወርክሾፕ ማዘጋጀት

   ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትና የሚመካከሩበት የውይይት መደረክና ወርክሾፕ ለማዘጋጀት በተያዘው እቅድ መሰረት በድምሩ አስር የተለያዩ ፎረምዎች ላለፉት አራት ሩብ አመታት በተሳካ ሁኔታ ተከናውነዋል፡፡

6. ለ9 የግል ዘር አባዥ ባለሃብቶች ስለ ዘር አመራረትና ንግድ ስራ የሙያ ስልጠና ተሰጥቷል።

7. አገር ውስጥና ውጭ አገር ከሚገኙ ተባባሪ ድርጅቶች ጋር የምርምር ትብብር ለመፍጠር ንድፈ ሀሳቦችን ማዘጋጀት

   የትብብር ንድፍ ሃሳብ አጻጻፍ ላይ ስልጠና ከተሰጠ በኋላ የስልጠናው ተሳታፊዎች 23 የምርምር ንድፈ ሃሳቦች ተዘጋጅተው ለገንዘብ ድጋፍ ጥየቃ ተልከዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ በአራተኛው ሩብ አመት ሁለት የሚሆኑ የምርምር ትብብር ንድፈ ሀሳቦች ለተባባሪ አካለት ተልከው፤ ውጤቱንም በመጠባበቅ ላይ ነን፡፡

8. ለነባር (LSB) ማህበራት የምርጥ ዘር አመራረት ክትትልና ድጋፍ አድርጎ ለገበያ የዘር ጥራት ማረጋገጫ አገልግሎት መስጠት

   ከሃረማየ ዩኒቨርሲቲ፣ምስራቅና ምእራብ ሀረርጌ ዞን ግብርና ጽ/ቤት በተዋቀረው የዘር ጥራት ቡድን አማካኝነት ለ12 ዘር አምራቾች ማህበራት ማሳ ላይ ክትትልና ግምገማ ተካሂዷል፡፡

9. ቅድመ  መስራች  ዘር ለማግኘት ከምርምር ተቋማት ጋር (ከፌዲስና ከሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ጭሮ ካምፓስ) በጋራ የዘር መረጣ ሙከራ(Participatory variety selection) በቦሎቄ፣በማሽላና በስንዴ ሰብሎች ላይ ተካሂዷል።
10. ለአራት ነባር (LSB) ማህበራት የኢንቨስትመንት ፈንድ ድጎማ ለማድረግ ታቅዶ ተጨማሪ በጀት ከ (CDI) በመፈቀዱ 1054984 ብር ድጉማ ተደርጓል፡፡ ይህ ድጎማ የተደረገው የአርሶአደር የዘር አማራች ማህበራትን አቅም የበለጠ ለማሳደግ እና የምርጥ ዘር ምርትን በብዛትና በጥራት ላማስፋፋት ነው፡፡ ይህ ድጎማ የተሰጣችው የዘር አማራች ማህበራት ቀርሳ፤ ራሬሆራ፤ ቢሻን ባቢሌ፤ ጡሎ ሲሆኑ ይህው ድጎማ የተሰጣቸው የባለድርሻ አካላት መቻራ ምርምር ማዕከል፤ ፌዲስ ምርምር ማዕከል፤ ኮምቦልቻ TVET ጭሮ ዩኒቨርሲቲ ካምፓስ፤ ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፤ ኦዳ ቡልቱም ዩኒየን እና CARE Ethiopia ምስራቅ ሐረርጌ ናቸው፡፡

11. በ ISSD ፓርትነርሽፕ ፕሮግራም ለሚሰሩ የዘር አመራረትና ጥራት ስራዎችና ለሌሎች ተዛማጅ ክንውኖች 1282900 ብር የገንዘብ ድጎማ ለተለያዩ በዘር አመራረትና ጥራት ስራዎች ላይ ለተሰማሩ አካላትተደርጓል፡፡

12. በተለዩ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከላት፤ የሰርቶ ማሳያ የምርምር ስራዎችን ማከናወን እና አርሶ አደሮችን ማማከር

በአመቱ በአጠቃላይ በታቀድው መሰረት በ6 የነበሩ እና 3 አዳዲስ የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት ላይ ማለትም በጭናክሰን፣ በሀረማያ፣ በቀርሳ፣ በጎሮ-ጉቱ፣ በዲሬ-ጥያራ፣ በድሬዳዋ አዋሌስራው በጃርሶ፣ባቢሌና ፌዲስ ተከናውኗል፡፡




13. በተመረጡ የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት ለሞዴል አርሶ አደሮችንና የልማት ጣቢያ ሰራተኞች ስልጠና ለመስጠት በተያዘው ዕቅድ መሰረት ከ8 ወረዳዎች ለተውጣጡ 130 ሙያተኞችና ሞዴል አርሶአደሮቾ በድንችና ስንዴ አመራረት እነዲሁም በማህበር አደረጃጀት ላይስልጠና ተሰጥቷል።
14. በገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት ከአርሶ አደሮችና ከሌሎች ባለድርሻ አከላት የተውጣጡ125 ተሳታፊዎች የተገኙበት ሁለት የመስክ ቀን በጭናክሰን፣ በጃርሶና በድሬ ጠያራ ተዘጋጅቷል።

15. ሰድስት (6) የእርሻና የድህረ ምርት የዘር ማቀነባበሪያ መሳሪያዎችን (የዘር ማበጠሪያና መውቅያ) ከአጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ለዘር አምራች ማህበራት ማቅረብ ተችሏል።
16. ሰባት (7)የውሃ መሳቢያ ሸራ ቱቦ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ለዘር አምራች ማህበራት ማቅረብተችሏል።

17. የዘር አምራች ማህበራት ምርጥ ዘር አምርተው ለህብረተሰቡ በማዳረስ ማህበረሰቡን ጠቅመው እነርሱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ማደራጀት፤ ማሰልጠን፤ ማብቃት በተያዘው እቅድ መሰረት በአራተኛው ሩብ አመት ሁለት ማህበራትን በጭሮ እና በጨርጨር ኦዳ ቡልቱም በማደራጀት በአመቱ የተደራጁትን ማህበራት ብዛት ስድስት ለማደረስ ተችሎአል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል በዩኒቨርሲቲያችን የምርምር ስርፀት ክፍል ወደ ዘር ማምራት ስራ የገቡት ስምንት ማህበራት ጥራቱን የጠበቀ ዘር እንዲያመርቱ ክትትል ተደርጎ 940.8 ኩንታል ተለያዩ ምርጥ ዘሮችን በዚሁ 2ኛ ሩብ ዓመት አምርቶ ለራሳቸውና ለአከባቢ ተጠቃሚዎች ሊያዘገጁ ችሎዋል፡፡

ሠንጠራዠ2: በዘር አምራች ማህበራትና የተዘሩ የተሸሻሉ የተሳያዩ የሰብል ዘሮች፣ የተሸፈነው የመሬት፣ የተሰራጨው የዘር መጠንና የተመረተው ምርት መጠን፡-

| ተ.ቁ | ወረዳ | የማህበሩ ስም/ ምርምር ጣቢያ | የተሸሻሉ የሰብል ዘር ዓይነት | ዝሪያ | የተሰራጨው የዘር መጠን (ኩታ) | የተሸሻፈና መሬት መጠን(ሄክታር) | የተገኘ ምርት | ምርት በሄ/ር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጭናክሳን | ሉጎ ማህበር | ስንዴ | ቀቀበ | 7.5 | 5.50 | 137.5 | 25.0 |
| 2 | ጃረሶ | አፈጉግ ቀ/ ማህበር | ስንዴ | ዲገሉ | 5.5 | 4.40 | 139.9 | 31.8 |
| | | አፈጉግ ቀ/ ማህበር | ስንዴ | ዳንዳኣ | 0.5 | 0.35 | 10.5 | 30.0 |
| 3 | ጎርጉቱ | ባሳ ቡቂስ | ስንዴ | ዲገሉ | 5.5 | 4.40 | 87.0 | 20.2 |
| | | | ስንዴ | ዳንዳኣ | 0.5 | 0.35 | 7.35 | 21.0 |
| 4 | ሜታ | አብዲ-ቦሩ | ስንዴ | ዲገሉ | 6.0 | 5.0 | 216 | 43.2 |
| 5 | ባቢሌ | ቁብሳ- አበዱልቃድር | ስውዝ | ሮባ | 5.0 | 5.0 | 70.0 | 14.0 |
| | | | | ወረር-961 | የረሳቸው | 2.5 | 30 | 12.0 |
| 6 | | ቢቂልቱ-ጉዲና | ስውዝ | ሮባ | 5.0 | 5.0 | 72.5 | 14.4 |
| | | | | ወረር-961 | የረሳቸው | 2.5 | 28.8 | 11.5 |
| 7 | ሀረሪ | ቂሌ | ስውዝ | ሮባ | 5.0 | 5.0 | 69 | 13.8 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | ወረር-961 | የረሳቸው | 2.5 | 27.25 | 10.9 |
| 8 | ድሬዳዋ | አዋሲ(ቢቂልቱ በሪ) | | ሮባ | 4.0 | 4.0 | 45 | 11.5 |
| | | ድምር | | | | | 940.8 | |

**ግብ 3.** የተገል,ጋዮችን/ደንበኞችን እርካታ እና የባለድርሻአካላትንተሳትፎ ማሳደግ

**ውጤት 1፡**ያደገ የባለድርሻአካላትተሳትፎ እና እርካታ

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. ገበያ-ተኮር ቴክኖሎጂዎችን መለየትና ለተጠቃሚ ማዘጋጀት

   ገበያ-ተኮር ቴክኖሎጂዎችን መለየትና ለተጠቃሚ ለማቅረብ በተያዘው እቅድ መሰረት በአዝእርት እና በእንስሳት ዘርፍ በርካታ ገበያ ተኮር ቴክኖሎጂዎች ተለይተው ተሰራጭተዋል፡፡

2. የድንች መጋዘን ከባለ ድረሻ አካላት ጋር መገንባት

   አራት የድንች መጋዘኖችን በኮምቦልቻ አን በሃረማያ ወረዳ ተሰርተው በመጠናቅ ላይ ሲሆን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደተመረጡ ማህበራት የማስተላለፍ ስራ ይከናወናል።



3. *ዓመታዊ የገበሬዎች እና ሌሎች የልማት አጋሮች የመስክ ቀን ማካሔድ*

**በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ተጨባጭ የምርምርና የመልካም ተመክሮ ማስፋፋት ውጤቶችን ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በመስክ ላይ በመገኘት ለማየትና ለመገምገም በሀብሮ፣በጉራዋ በኮምቦልቻ በባቢሌ፣ በሐረማያ፣ ጉባ ቆርቻ ወረዳዎች የአርሶአደሮችና የሌሎች ባለድርሻ አካላት የመስክ ቀን ተካሂዷል፡፡በተጨማሪም በሁለተኛው ሩብ ዓመት በሚኤሶ፣በሃብሮ፣በቀርሳ፣በሜታ፣በሐረማያ ወረዳዎች ተካሂደዋል።**






Groundnut
Production
packag
Research





**ግብ 4.** ከምርምር ቴክኖሎጂዎችና ተረፈ ምርቶች የሚገኙ

**ውጤት 1፡**ያደገ የተሰበሰበ የገቢ መጠን

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. ከምርምር ቴክኖሎጂዎችና ተረፈ ምርቶችን 1350000 ብረ ገቢ ተገኝቷል። ይህም የተገነው ከድቃይ ፍየሎች፣ ከምርት ዘር ሽያጭ፤ ከተለያዩ አትክልትና ፍራፍሬዎች፣ ከቀንድ ከብት ሽያጭ ነው፡፡

**ግብ 5.** የግብኣት አጠቃቀምን ማሻሻል

**ውጤት 1፡**የተሻሻለ የግብኣት አጠቃቀም

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. የምርምር ፈንዶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋላቸውን ለመከታተል ጥረት ተደርጓል፡፡

**ግብ 6.** የስራ ሂደቶችን ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ ማድረግ

**ውጤት 1፡**ውጤታማነቱና ወጪ ቆጣቢነቱ የጨመረ የምርምር ስርዓት

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. የምርምር ትኩረት መስኮችን መሰረት በማድረግ ስድስት የምርምር ቡድኖችን የተዋቀሩ ሲሆን ለምርምር ቡድኖቹም አስተባባሪዎች ተመድበዋል፡፡
2. ተከታታይ በስራ ላይ ስልጠና ተሰጥቶአል፡፡

**ግብ 8.** የክትትል፣ የግምገማናየድጋፍ ስርዓትን መዘርጋትና ማጠናከር

**ውጤት 1:**የተሻሻለ የክትትል፣ የግምገማና የድጋፍ ስርዓት

**ዋና ዋና ተግባራት:**

1. ለምርምርና ስርጸት ተግባራት ወቅቱን የጠበቀ ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ ተደርጓል፡፡
2. በመስክና ቴክንክ ረዳት ደረጃ የምርምርና ስርጸት የስራ ግምገማ ተደርጓል፡፡
3. በዳይሬክተርና በምርምር ቡድኖች ደረጃ የምርምርና ስርጸት የስራ ግምገማ ተደርጓል፡፡

**ግብ 9.** ፕሮግራሞችን፣ የምርምር ውጤቶችን እና አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ

**ውጤት 1:**የተዋወቁ የምርምር ውጤቶች እና አገልግሎቶች

**ዋና ዋና ተግባራት:**

1. የምርምር ሥራዎች እና የምርምር ውጤቶችን ለማስተዋወቅ ከሃረማያ ዩኒቨርሲቲ ማህረሰብ ሬዲዮ ጋር በመቀናጀት የተለያዩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት እንዲዘገብና እንዲጠናቀር ተደርጓዋል፡፡ በተጨሪም የምርምር ውጤቶችን የሚያስተዋውቁ በርካታ በራሪ ጽሁፎችን፤ ፖስተሮችን ባነሮችን፤ መጽሄቶችን በተለያዩ ቋንቋዎች በማዘጋጀት ለማሰራጨት ተችሏል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከፋና ኤፍ ኤም ሬዴዩ ጋር በመተባባር ለአርሶ አደሩ የሚተላለፍ ቴክኖሎጂ ነክ ዜናዎች በየሳምንቱ በኦሮሚኛ ቋንቋ ማስተላለፍ ስራ ተጀምሮአል፡፡

**ግብ 10.** ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትና ማዘመን

**ውጤት 1:**የተስፋፋና የተቋቋመ ፋሲሊቲ

**ዋና ዋና ተግባራት:**

1. የምርምርና የቴክኖሎጅ ሽግግር ስራዎችን በተሳለጠ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል አንድ ራሱን የቻለ የህንጻ ኮምፕሌክስ (ዘመናዊ የምርምር ላቦራቶሪ፤ የምርምር ቢሮዎች፤ የህትመትና የምርምር ጹህፍ ማደራጃ ቦታዎች፤ የመረጃ ቋት ክፍሎች፤የአውደ ጥናት አዳራሾች እና ሙዚየም ያካተተ) ግንባታ ለማከናወን በባለሙያዎች ላማስጠናትና ዲዛይኑን ለማሰራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት የተደረገ ሲሆን፡፡ የበጀት ጥያቄ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ቀርቦአል፡፡
2. ከተለያዩ ቦታዎች ለምርምርና ስርጸት ስራዎቸ ተገዝተው ለሚመጡ ፍየሎችና በጎች ማቆያ ቤት(quarantine)ለመስራት የቦታ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

**ግብ 11.** የአመራር የስራ ብቃትን፣ፍትሃዊነትን፣ እና ተነሳሽነትን ማሳደግ እና ፆታን ያማከለ አሰራር ማስፈን

**ውጤት 1፡**የተሻሻለ የሰራተኞች እና ተቋማዊ አፈፃፀም

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. ለመምህራን የምርምር  የንድፈ ሃሣብ አዘገጃጀት ስልጠና መስጠት

   ከተለያዩ ኮሌጆች ለተውጣጡ 20 መምህራን የንድፈ ሃሳብ አዘገጃጀት ላይ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

2. የመረጃ አያያዝና ትንተና ስልቶች ላይ ስልጠና መስጠት ለ90 መምራን በ ስድስት ዙሮች የተለያዩ የመረጃ አያያዝና ትንተና ስልጠና ተሰጥቶአል፡፡
3. ለምርምር የቴክኒክና የመስክ ረዳቶች  በመረጃ አያያዝና አጠናቀር አጫጭር ስልጠናዎችን ለ80 ቴክኒክ ረዳቶች የአመንዣኪ እንስሳት አያያዝና አጠባበቅ ተሰጥቶአል፡፡
4. በምርምርና ስርጸት ስር በሚደረጉ የስልጠናና የአቅም ግንባታ ስራዎች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ለማጎልበት ቢያንስ 5% ሴቶች እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡

**ግብ 12.** በመልካም ተመክሮዎች ዙሪያ የልምድ ልውውጥ ማድረግና የስራ ፈጠራ ክህሎትና አስተሳሰብን ማሳደግ

**ውጤት 1፡**ያደገ የስራ ፈጠራ ክህሎትና አስተሳሰብ፤የተተገበረ መልካም ተሞክሮ

**ዋና ዋና ተግባራት፡**

1. ወደ 71 የሚሆኑ የዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎች/መምህራን በሃገር ውስጥ የሙያ ማህበራትና ሌሎች ኮንፈረንሶች ላይ እንዲሳተፉና የምርምር ግኝታቸውን እንዲያቀርቡ እገዛ ተደርጎላቸዋል፡፡
2. በአስር የተለያዩ ቡድኖች የተዋቀሩ ተመራማሪዎችና ሌሎች የምርምር ሰራቶኞች በሐገሪቱ ውስጥ የሚገኙ  የተሌዩ የምርምር ማእከላትን እና ዩኒቨርሲቲዎችን ጎብኝተው  የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማስቻል

# ክፍል 2፡ የተለኩ የፊዚካል ስራዎች የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

በምርምር ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት ቢሮ ስር ለ2007 ዓ.ም. የታቀዱ ተግባራት የአራተኛ ሩብ አመት ክንውን ና የአመቱ አጠቃላይ አፈፃፀም

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶ ኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | ገበያ ተኮር ፕሮግራሞችን፣ ውጤቶችንና አገልግሎቶችን ማሳደግ | 29 | ፍላጎት ተኮር የምርምር ፕሮግራሞችን፣ ተግባራትን፣ ውጤቶችን እና አገልግሎቶችን ማሳደግ | የጨመረ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ቴክኖሎጂዎችና አገልግሎቶች እና ያደገ የደንበኞች እርካታ | በዩኒቨርሲቲው የገንዘብ ድጋፍ በመካሄድ ላይ ያሉ የምርምር ስራዎችን ሪፖርት (ሳይንሳዊ ውጤቱን) ማቅረብ (የ2005 ዓ.ም ድጋፍ) | ቁጥር | 36 | - | - | - | 36 | 36 | 100 | |
| | | | | | በዩኒቨርሲቲው የገንዘብ ድጋፍ በመካሄድ ላይ ያሉ የምርምር ስራዎችን ማጠናቀቅ (የ2006 ዓ.ም ድጋፍ) | ቁጥር | 51 | - | - | 0 | - | - | - | ሪፓርቶች ጨርሰው የሚገቡት በሚቀጥለው አመት ስለሆነ፡ ፡ |
| | | | | | በሲዳ (SIDA) የገንዘብ ድጋፍበግብርና ሳይንስ መስክ በመካሄድ ላይ ያሉ የምርምር ስራዎችን ሪፖርት (ሳይንሳዊ ውጤቱን) ማቅረብ (የ2005 ዓ.ም ድጋፍ) | ቁጥር | 13 | - | - | - | 13 | 13 | 100 | |
| | | | | | ለ2007 ዓ.ም. በጀት ለውድድር የሚቀርቡ የምርምር ንድፈ ሃሣቦችን መጋበዝና በግልጽ መስፈርቶች ላይ ተመስርቶ የንድፈ ሃሣቦችን መረጣ ማካሄድና የምርምር ገንዘብ ድጋፍ ሰጥቶ ስራን ማስጀመር | ቁጥር | 100 | - | - | - | 100 | 107 | 107 | |
| | | | | | ለ2007 ዓ.ም ለውድድር ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ያለፉ የምርምር ንድፈ ሃሣቦች የሚቀርቡበትን | ቁጥር | 6 | - | - | - | 6 | 6 | 100 | |

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | | | | | መደረክ ማዘጋጀት | | | | | | | | | |
| | | | | | በኢትዩጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የገንዘብ ድጋፍ በግብርና ሳይንስ መስክ በመካሄድ ላይ ያሉ የምርምር ስራዎችን ማከናወን፡፡ | ቁጥር | 128 | 128 | 128 | 100 | 128 | 128 | 100 | |
| | | | | | የተለያዩ የምርምር ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ የምርምር ድጋፍ ማስገኘት | የፕሮጀክት ብዛት | 5 | 1 | 1 | 100 | 4 | 4 | 80 | ሌሎች ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ውጤታቸው በመጠባቅ ላይ ያሉ አሉ። |
| | | | | | ለዝርያ ልቀት ደርሰው በሂደት ላይ የሚገኙትን የምርምር ስራዎች ማጠናቀቅና ለብሄራዊ ዘር አጽዳቂ ኮሚቴ ማቅረብ፡፡ | ቁጠር | 3 | - | - | - | 3 | 3 | 100 | ከቀረቡት ዝርያዎች ማካከል አንድ የማሽላ ዝርያ ጸድቆ ተለቋል። |
| | | | | | በምስራቅ ኢትዮጵያ ውስጥ እስከ አሁን በዩኒቨርሲቲው የተሠራጩ ቴክኖሎጅዎችን ቅቡልነት፣ ያሉበትን ደረጃ እና ተግዳሮቶችን መዳሰስ | ቁጥር | 1 | - | - | 0 | 1 | 1 | 60 | የመረጃ መተንተን ስራ ተጀምሮአል፡፡ |
| | | | | | በምስራቅ ኢትዮጵያ በአራት ወረዳዎች ውስጥ የስንዴ ቴክኖሎጂ ቅቡልነት ላይ የዳሳሳ ጥናት ማካሔድ | ቁጥር | 1 | - | - | 0 | 1 | 0 | 0 | በጅት በወቅቱ ባለመድረሱ |
| | | | | | ለ2008 ዓ.ም. በጀት ለውድድር የሚቀርቡ የምርምር ንድፈ ሃሣቦችን ለውድድር መጋበዝ | የጥሪ ቁጥር | 1 | - | - | - | 1 | 1 | 100 | 341 የምርምር ንድፈ ሀሳቦት ገብተዋል |
| | | | | | ለ2008 ዓ.ም. በጀት ለውድድር ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ያለፉ የምርምር ንድፈ ሃሣቦችን የሚቀርቡበት መድረክ ማዘጋጀት | የመድረክ ቁጥር | 6 | 6 | 6 | 100 | 6 | 6 | 100 | 240 የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማ ያለፉ ንድፈ ሀሳቦች ለሁለተኛ ዙር ግምገማ |

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | | | | | | | | | | | | | | ቀርበዋል፡፡ |
| | | | | | 32ኛ አመታዊ የምርምር እና ስርፀት ጉባኤ በስድስቱ የምርምር የትኩረት አቅጣጫዎች ማካሔድ | ቁጥር | 1 | | | 100 | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | በወቅታዊ ሁኔታዎች ላይ ያተኮሩ ኮንፈርነሶችን በኮሌጆች ጥያቄ መሰረት ማካሄድ | የኮንፈረንስ ቁጥር | 3 | 2 | 3 | 150 | 3 | 5 | 166 | |
| | | | | | የተሻሻሉ የስኳር ድንች ዘር ችግኝ (ቁርጥራጭ) ስርጭት ስራ ማከናወን | ቁርጥራጭ | 1.2 ሚሊየን | 400000 | 0 | 0 | 400000 | 1675000 | 419 | |
| | | | | | በህብረተሰብ ተሳትፎ በተፋሰስ ላይ የተሰሩ የአፈርና የውሀ እቀባ በገጸ ምድር የዛፍ ችግኞችን መትከል፡፡ | የተፋሳስ ቁጥር | 2 | - | - | - | 2 | 2 | 100 | |
| | | | | | የፍራፍሬና ዘርፈብዙ (Multi-purpose) ጥቅም ያላቸውን የዛፍ ዝሪያዎችን በመኖሪያ አካባቢና በእርሻ ቦታዎች ማስተከል | የተጠሚ ቁጥር | 40 | 0 | 0 | 0 | 40 | 95 | 237.5 | |
| | | | | | የ2012/13 (30ኛ) የምርምርና ስርፀት ፕሮሲዲንግ ህትመትን ማጠናቀቅ | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | የ2013/14 (31ኛ) የምርምርና ስርፀት ፕሮሲዲንግ ህትመትን ማጠናቀቅ | ቁጠር | 1 | 1 | 0 | - | | | | ሪፓርት ስላልገባ፡፡ |
| | | | | | የተሻሻሉ የቲማቲም፤ የበቆሎ፤ የስንዴ፤የባቄላ፤ የስኳር ድንች አመራረት እንዲሁም የሰብሎችን የአጣምሮ መዝራትኤክስቴንሽን መመሪያዎችን (Manuals) ማዘጋጀት | ቁጥር | 8 | 8 | 0 | 0 | 8 | 8 | 100 | መመሪዎች ተዘጋጅተው ለህትመት በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡ |

| እይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | እቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | እቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | | | | | የ Bio-diversity ወርክሾ ኘሮሲዲንግ ማሳተም | ቁጥር | 1 | 0 | - | - | 1 | 0 | 0 | የመጨረሻ ደረጃ ስራ በመሰራት ላይ ሲሆን ለህትመትም እየተዘጋጀ ነው፡፡ |
| | | | | | በተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ፤ በእንስሳት ሳይንስ በዕጽዋት ሳይንስ እንዲሁም በግብርና ምጣኔ ሀብት የትምህርት መስኮችየማስተርስ መመረቂያ ድርሳናትን አብስትራክት 4 ጥራዝ በሙያ መስክ ማሳተም | ቁጥር | 4 | 0 | - | - | 4 | 4 | 100 | |
| | | | | | የተሻሻሉ የበቆሎና የድንች ቴክኖሎጅዎችን የፓይለት ማስፋፋት (Pilot-scaling) ስራ መስራት | የአርሶ አደር ቁጥር | 240 | 0 | 0 | 0 | 240 | 243 | 101.3 | |
| | | | | | የተለያዩ ሳይንሳዊ የምርምር መጣጥፎችን (articles) በሚገመገሙ (Peer-reviewed) ጆርናሎች እንዲታተሙ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ | ቁጥር | 15 | 5 | 3 | 60 | 15 | 5 | 33 | አግባብ ያለው ጥያቄ ባለበቅረቡ |
| | | | | | የምርምር ፖሊሲና መመሪያ ሰነድ ዝግጅት ማጠናቀቅ | ቁጥር | 2 | 0 | - | 100 | 2 | 2 | 100 | |
| | | | | | East African Journal of Sciences 6ኛ (2012)እትም ቁጥር ሁለት ማሳተም | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | East African Journal of Sciences 7ኛ(2013)እትም ማሳተም | ቁጥር | 2 | - | - | 100 | 2 | 2 | 100 | |
| | | | | | East African Journal of Sciences 8ኛ(2014)እትም ማሳተም | ቁጥር | 2 | 1 | 1 | 100 | 2 | 1 | 50 | የቀረው እትም በመጠናቀቅ ላይ ነው፡፡ |
| | | | | | የ East African Journal of Sciences ድረ ገጽ (online submission and review) ማዘጋጀትና ስራ ማስጀመር | በፐርሰንት | 100 | 0 | 0 | 0 | 100 | 100 | 100 | |

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡክብደትበመቶ ኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | | | | | በ East African Journal of Sciences እንዲታተሙ የሚቀርቡ ሳይንሳዊ መጣጥፎችን (Manuscripts) በባለሙያዎች ማስገምገም | የመጣጥፍ ቁጥር | 160 | 40 | 40 | 100 | 160 | 120 | 75 | ገምጋሚዎች የተላከላቸውን መጣጥፍ በወቅቱ ገምግመው ባለመመለሳቸው ምክንያት |
| | | | | | የህትመት መመሪያ መዘጋጀት፡፡ | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | የምርምር ፖሊሲ እና መመሪያ ሰነድ ማሳተም፡፡ | ቁጥር | 2 | 2 | 0 | 0 | 2 | 0 | 0 | የህትመት ስራ ብቻ ቀርቶታል፡፡ |
| | | | | | የዩኒቨርሲቲውን የምርምር የትኩረት መስኮችን ሰነድ ማሳተም | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል ከተመራማሪዎች በቀረበየምርምርእይታና የማህበረሰቡን ፍላጎት ባማከለ ሁኔታ ምርምር እያካሄደ ሣይንሳዊ ጽሁፎችንና ችግር ፈቺ ቴክኖሎጅዎችን ማቅረብ | የምርምር ጹህፍ ብዛት | 10 | 5 | 0 | 0 | 10 | 8 | 80 | |
| | | | | | በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል በተጠናቀረ መረጃ ተመራማሪዎች የምርምር ስራ ይሰሩ ዘንድ የይፋ ጥሪ ማድረግ | ቁጥር | 1 | | | | 1 | 1 | 100 | ሂደቱ በሩብ አመት መሆኑ ቀርቶ ሁሌም የሚፈልግ ሰው መረጃውን ማግኘት ወደሚችልበት ሂደት ተለውጦአል |
| | | | | | በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል ሰለሚከናወኑ የምርምር ስራዎች በአካባቢው ለሚገኙ የማህበረሰብ አባላትና ለሌሎች ባለ ድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማካሄድ | የውይይት መድረክ | 2 | 1 | 1 | 100 | 2 | 2 | 100 | |

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡክብደትበመቶ ኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | | | | | በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል ወቅታዊ የጤና መረጃዎችና የምርምር ውጤቶችን እያዘጋጀ ለተጠቃሚዎች የሚያሰራጭ ክፍል በማቋቋም በሰው ኃይልና በማቴሪያል ማደራጀት | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | አስፈላጊ የማቴሪያል ግብአቶች ተገዝተው የገቡ ሲሆን የሰው ሐይል በቅጥር ሂደት ላይ ነው:: |
| | | | | | በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል በአመት አንድ ግዜ የስነ ህዝብና ጤና ቡሌቲን ማሳተም | ቁጥር | 1 | 1 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | መጣጥፎቹ ተዘጋጅተው ለህትመት በዝግጅት ላይ ናቸው:: |
| | | | | | በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል የሚወጣ ኒውስሌተር (Newsletter) ማዘጋጀት | ቁጥር | 2 | 1 | 0 | - | 2 | 1 | 50 | |
| | | | | | በቀርሳ ዲሞግራፊክ ማእከል በሚሰሩ የምርምረ ስራዎችን በመጠቀም የፖሊሲ መነሻ ሀሳብ ማዘጋጀት እና ጠቃሚ መረጃዎችን ማውጣት | ቁጥር | 2 | 1 | 3 | 300 | 2 | 8 | 400 | ብዙ መምህራንን በማሳተፍ ስለተሰራ |
| | | | | | ነባር ኢንስቲቲዩቶችን መልሶ የማዋቀርና ስራ የማስጀመር እንዲሁም አዲሶችን ለማቋቋም የሚረዳ መመሪያ ማዘጋጀት | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | ለተለያዩ የሰብል ዝርያዎቸ የዘር ገበያ መለየትና የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ | የጥናት ቁጥር | 1 | - | - | - | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | የገበያ ትስስርን ለመፍጠርና የዘር ግብይትን ለማሳለጥ አጋሮችን  መለየት | የአጋር ቁጥር | 2 | 0 | 0 | 0 | 2 | 2 | 100 | |
| | | | | | የተለያዩ የብድርና ቁጠባ አገልግሎት ስጪ ተቋማትን መለየትና ከዘር አምራች ማህበራት ጋር ትስስር | የአውደ ጥናት ብዛት | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 100 | |

| እይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡክብደትበመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | እቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | እቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | | | | | እንዲፈጥሩ አውደ ጥናት ማካሄድ | | | | | | | | | |
| | | | | | የንብ እርባታ የአርሶአደሮች የምርምር ቡድን ማቋቋም | የምርምር ቡድን ቁጥር | 1 | 0 | - | - | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | የተሸሻሉ የዶሮ ዝርያዎችን ለተመረጡ ሴት አርሶ አደሮች ማሰራጨት | ቁጥር | 40 | 0 | 0 | 0 | 40 | 40 | 100 | |
| | | | | | የመልካም ተመክሮና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማላመድ ማስተዋወቅና ማስፋፋት | የቴክኖሎጅቁጥር | 17 | 4 | 4 | 100 | 17 | 23 | 135 | |
| | | | | | የተሸሻሉ የሰብል ዘሮች ብዜት ስራ ማከሄድ | በሄክታር | 8.5 | 0 | 6 | - | 8.5 | 28.7 | 338 | |
| | | | | | የተሻሻሉ የሰብል ዘሮችን ለተጠቃሚዎቸ ማሰራጨት | በኩንታል | 650 | 200 | 675 | 337.5 | 650 | 1214 | 187 | ከእቅድ በላይ ስለተመረተ ስርጭቱም በዚያው ልክ ተሰራጭቷል |
| | | | | | አዲስ የተለቀቀውን የካሮት ዘር ማባዛት | በኪ.ግ | 100 | 100 | 20 | 20 | 100 | 20 | 20 | |
| | | | | | አዲስ የተለቀቀውን የነጭ ሽንኩርት ዘር ማባዛት | በኪ.ግ | 1000 | 1000 | 20 | 20 | 100 | 20 | 20 | |
| | | | | | ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት ቴክኖሎጂን መስራት | ቁጥር | 50 | 10 | 30 | 300 | 50 | 49 | 98 | |
| | | | | | ተንቀሳቃሽ የዶሮ ቤት ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅ ማስፋፋት | ቁጥር | 50 | 10 | 31 | 310 | 50 | 49 | 98 | |
| | | | | | የተሸሻሉ የዶሮ ዝሪያዎችን ማስተዋወቅ | የዶሮ ቁጥር | 50 | 10 | 22 | 220 | 50 | 77 | 154 | ምቹ ኢጋጣሚ ስለተፈጠረ |
| | | | | | የተሸሻሉ የንብ ቀፎዎችንና የማነብ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅ | የቀፎቁጥር | 20 | - | 3 | 0 | 20 | 13 | 65 | |

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | | | | | | | | ማብራሪያ/ ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | |
| | | | | | | | የዓመቱ | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | | | | | የተሻሻሉ የፍየልና/የበግ ዝሪያዎችን ማስተዋዋቅ | ቁጥር | 100 | 40 | 40 | 100 | 100 | 100 | 100 | |
| | | | | | ለእንስሳት መኖ የሚሆኑ የተሻሻሉ የተክል ዝሪያዎችን ማስተዋዋቅና ማስፋፋት | የዝርያ ቁጥር | 3 | 0 | 1 | 0 | 3 | 4 | 133 | |
| | | | | | ስትራቴጂክ ምርምር የአዳቃይ ዘር ብዜት እና እደሳ ስራ ማከናወን (germplasm regeneration, maintenance and multiplication) | የዝርያ ቁጥር | 14 | 0 | 0 | 0 | 14 | 14 | 100 | |
| | | | | | የተሻሻሉ ጊደሮችን ለተመረጡ ሴት አርሶ አደሮች ማሰራጨት | ቁጥር | 20 | 0 | 0 | 0 | 20 | 25 | 125 | ምቹ አጋጣሚ በመፈጠሩ |
| | አጋርነትን ማሳደግ | 6 | የምርምር አጋርነትንና ትስስርን ማሳደግ | የጨመረ የአጋሮች ብዛት | ምርምር የሚሹችግሮችን በቀጣይነት ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መለየት፣ የምርምር ንድፈ-ሃሳብ መቅረጽ | ቁጥር | 2 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | የሴቶችን የልማት ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ማጎልበት | ከተሳታፊዎች በመቶኛ | 10 | 10 | 10 | 100 | 10 | 10 | 100 | |
| | | | | | ለወረዳ ሙያተኞች፣ ለልማት ሰራተኞች፣ ለአርሶ አደሮችና ሌሎች ባላድርሻ አካላት በግብርና በጤና በሕግ እና ሌሎች መስኮች ስልጠና መስጠት | የሰልጣኞች ቁጥር | 1050 | 120 | 100 | 83 | 1050 | 855 | 81.4 | |
| | | | | | በ(LSB) ሞዴል የማስፋፋት ስራ ላይ ለሚሳተፉ አጋሮች በግምገማና ክትትል፣ ግብይት፣ አደረጃጀትና ተጨማሪ ዘር እሴት ላይ ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ብዛት | 21 | 0 | 0 | 0 | 21 | 70 | 333 | |

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | እቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | እቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | | | | | ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበትና የሚመካከሩበት የውይይት መደረክና ወርክሾፕ ማዘጋጀት | ቁጥር | 8 | 3 | 2 | 67 | 8 | 10 | 125 | |
| | | | | | ለግል ዘር አባዥ ባለሃብቶች ስለ ዘር አመራረትና ንግድ ስራ የሙያ ስልጠና መስጠት | የስልጠና ቁጥር | 2 | 1 | 0 | 0 | 2 | 9 | 450 | |
| | | | | | አገር ውስጥና ውጭ አገር ከሚገኙ ተባባሪ ድርጅቶች ጋር የምርምር ትብብር ለመፍጠር ንድፈ ሀሳቦችን ማዘጋጀት | ቁጥር | 12 | 2 | 2 | 100 | 12 | 23 | 192 | ምቹ አጋጣሚ በመፈጠሩ |
| | | | | | የልማት አማካሪ ካውንስል አውደ ጥናት ላይ መሳተፍና ሪፓርት ማቅረብ፡፡ | ቁጥር | 3 | 1 | 0 | | 3 | 0 | 0 | ስላልተጋበዝን |
| | | | | | ለነባር (LSB) ማህበራት የምርጥ ዘር አመራረት ክትትልና ድጋፍ አድርጎ ለገበያ የዘር ጥራት ማረጋገጫ አገልግሎት መስጠት | የአገልግሎት ብዛት | 16 | 4 | 4 | 100 | 16 | 16 | 100 | |
| | | | | | ቅድመ መስራች ዘር ለማግኘት ከምርምር ተቋማት ጋር በጋራ የዘር መረጣ ሙከራ ማካሄድ (Participatory variety selection) | የሙከራ ብዛት | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 3 | 300 | |
| | | | | | ለአራት ነባር (LSB) ማህበራት የኢንቨስትመንት ፈንድ ድጎማ ማድረግ | ብር | 120 ሺ | 0 | 0 | 0 | 120 ሺ | 1054984 | 879 | ተጨማሪ በጀት ከ (CDI) በመፈቀዱ ክንውኑ ሊጨምር ችሏል ፡፡ |
| | | | | | በ ISSD ፓርትነርሽፕ ፕሮግራም ለሚሰሩ የዘር አመራረትና ጥራት ስራዎችና | ብር | 897 130 | 224283 | 451,000 | 201 | 897130 | 1,282,900 | 143 | |

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | | | | | ለሌሎች ተዛማጅ ክንውኖች የገንዘብ ድጎማ ማድረግ | | | | | | | | | |
| | | | | | በተለዩ የገበሬ ማሰልጠኛ ማእከላት፤ የሰርቶ ማሳያ የምርምር ስራዎችን ማከናወን እና አርሶ አደሮችን ማማከር | የማዕከላት ቁጥር | 15 | 0 | 9 | 0 | 15 | 18 | 120 | |
| | | | | | በተመረጡ የገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት ለሞዴል አርሶ አደሮችንና የልማት ጣቢያ ሰራተኞች ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ቁጥር | 90 | - | - | 155.6 | 90 | 130 | 144.4 | |
| | | | | | በገበሬ ማሰልጠኛ ማዕከላት ለአርሶ አደሮችና ለሌሎች ባለድርሻ አከላት የመስክ ቀን ማዘጋጀት | በቁጥር | 3 | 1 | 0 | 0 | 3 | 2 | 67 | |
| | | | | | የእርሻና የድህረ ምርት የዘር ማቀነባበሪያ መሳሪያዎችን ከአጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ለዘር አምራች ማህበራት ማቅረብ | ቁጥር | 4 | 0 | 0 | 0 | 4 | 6 | 150 | |
| | | | | | የውሃ መሳቢያ ሸራ ቱቦ ከአጋር ድርጅቶች ጋር በቅንጅት ለዘር አምራች ማህበራት ማቅረብ | ጥቅል | 15 | 0 | 0 | 0 | 15 | 7 | 46.7 | የግብአት ዋጋ መናር |
| | የተገልጋዮችን /ደንበኞችን/ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎና እርካታ | 10 | የተገልጋዮችን/ደንበኞችን እርካታ እና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማሳደግ | ያደገ የባለድርሻ አካላትተሳትፎ እና እርካታ | ገበያ-ተኮር ቴክኖሎጂዎችን መለየትና ለተጠቃሚ ማዘጋጀት | ቁጥር | 3 | 1 | 1 | 100 | 3 | 3 | 100 | |
| | | | | | የዘር አምራች ማህበራት ምርጥ ዘር አምርተው ለህብረተሰቡ በማዳረስ ማህበረሰቡን ጠቅመው እነርሱም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ማደራጀት፤ | የተደራጁ ቁጥር | 6 | 2 | 2 | 100 | 6 | 6 | 100 | |

| ኢይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | ማሳደግ | | | | ማሰልጠን፣ ማብቃት | | | | | | | | | |
| | | | | | የድንች መጋዘን ከባለ ድረሻ አካላት ጋር መገንባት | ቁጥር | 2 | 0 | 4 | 0 | 2 | 4 | 200 | ፕሮጀክቶች ድጋፍ በማድረጋቸው |
| | | | | | ዓመታዊ የገበሬዎች እና ሌሎች የልማት አጋሮች የመስክ ቀን ማካሔድ | ቁጥር | 12 | 1 | 0 | 0 | 12 | 13 | 108 | |
| የፋይናንስ/የበጀት ኢይታ | ገቢን መጨመርና የገቢ ምንጬችን ማስፋት | 4 | ከምርምር ቴክኖሎጂዎችና ተረፈ ምርቶች የሚገኙ ገቢዎችን መሰብሰብ | ያደገ የተሰበሰበ የገቢ መጠን | የምርምር ቴክኖሎጂዎችና ተረፈ ምርቶችን የገቢ ምንጭ እንዲሆኑ ማስቻል | ብር | 1000 000 | 400000 | 445000 | 111.3 | 1000 000 | 1350 000 | 134.5 | |
| | የግብአት አጠቃቀምን ማሻሻል | 3 | የግብኣት አጠቃቀምን ማሻሻል | የተሻሻለ የግብኣት አጠቃቀም | የምርምር ፈንዶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋላቸውን መከታተል | የግምገማ ቁጥር | 2 | 1 | 1 | 100 | 2 | 2 | 100 | |
| የውስጥ አሰራር ሂደት ኢይታ | የስራ ሂደቶችን ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ ማድረግ | | የስራ ሂደቶችን ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ ማድረግ | ውጤታማነቱና ወጪ ቆጣቢነቱ የጨመረ የምርምር ስርዓት | የመወሰን ዓቅምን ማሳደግና ያልተማከለ አሰራርን ማስፈን | የውይይት መድረክ | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | የምርምር ትኩረት መስኮችን መሰረት በማድረግ የምርምር ቡድኖችን ማዋቀር | ቁጥር | 6 | 0 | 0 | 0 | 6 | 6 | 100 | |
| | | | | | የስራ ላይ ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ብዛት | 50 | 0 | 0 | 0 | 50 | 50 | 100 | |

| እይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | የዓመቱ | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | በስራ ውጤት ላይ የተመሰረተ ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | 36 | በስራ ውጤት ላይ የተመሰረተ ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት | ያደገ የሽልማት ና የማበረታቻ ስርዓት | በምርምር ስራቸው የላቀ ውጤት ለሚያስመዘግቡ ተመራማሪዎች፤የቴክኒክና የመስክ ረዳቶች፤የባለድርሻ አካላት፤ ኮሌጆች/ትምህርት ቤቶች/ ዲፓርትመንቶች የሽልማት/ማበረታቻ አሰጣጥ ደንብ ማዘጋጀት | ቁጥር | 1 | 0 | 1 | 0 | 1 | 1 | 100 | ለውውይይት ማቅረብ ይቀረዋል፡፡ |
| | | | | | በምርምርና በቴክኖሎጂ ስርጸት ስራዎቻቸው የላቀ ተሳትፎ ላደረጉ ተመራማሪዎች እና የስርጸት ባለሙያዎች በመሸለም ዕውቅና መስጠት | የሽልማት ብዛት | 3 | 3 | 0 | 0 | 3 | 0 | 0 | ደንቡ ስላልተጠናቀቀ |
| | | | | | የምርምርና ስርጸትስራዎችን በአግባቡና በተምሳሌትነት መምህራንን ዕያስተባበሩና እያሳተፉ በመስራት ወጤታማ ሆነው በቴክኖሎጂ ልቀት የላቁ ኮሌጆችን/ትምህርት ቤቶችን/ ዲፓርትመንቶችን መሸለም | የሽልማት ብዛት | 3 | 3 | 0 | 0 | 3 | 0 | 0 | ደንቡ ስላልተጠናቀቀ |
| | | | | | በውጤታማነታቸው ብልጫ ላሳዩ የቴክኒክና የመስክ ረዳቶች የማበረታቻ ሽልማቶችን መስጠት | የሽልማት ብዛት | 6 | 6 | 0 | 0 | 6 | 0 | 0 | ደንቡ ስላልተጠናቀቀ |
| | | | | | በውጤታማነታቸው ብልጫ ላሳዩ ባለድርሻ አካላት የማበረታቻ ሽልማቶችን መስጠት | ቁጥር | 6 | 0 | 0 | 0 | 6 | 4 | 66.7 | |
| | የክትትልና የግምገማ ስርዓትን | | የክትትል፣ የግምገማናየድጋፍ ስርዓትን መዘርጋትና ማጠናከር | የተሻሻለ የክትትል፣ የግምገማና የድጋፍ ስርዓት | ለምርምርና ስርጸት ተግባራት ወቅቱን የጠበቀ ክትትል፣ ግምገማና ድጋፍ ማድረግ | ቁጥር | 4 | 1 | 1 | 100 | 4 | 4 | 100 | |
| | | | | | በመስክና ቴክንክ ረዳት ደረጃ የምርምርና ስርጸት የስራ ግምገማ ማድረግ | ቁጥር | 4 | 1 | 1 | 100 | 4 | 4 | 100 | |

| እይታ | ከተቋም ወደ ስራ ክፍሉ የወረዱ ስትራቴጂያዊ ግቦች | የግቡ ክብደት በመቶኛ | በስራ ክፍሉ ደረጃ ተመንዝረው የተቀመጡ ስትራቴጂያዊ ግቦች | ከስትራቴጂያዊ ግቡ የሚጠበቅ ውጤት | ስትራቴጂያዊ ግቡን ለማሳካት የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት | መለኪያ | የዓመቱ | የ4ኛ ሩብ ዓመት | | | የአመቱ | | | ማብራሪያ/ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | አቅድ | ክንውን | ክንውን (%) | |
| | መዘርጋት/ማጠናከር | | | | በዳይሬክተርና በምርምር ቡድኖች ደረጃ የምርምርና ስርጸት የስራ ግምገማ ማድረግ | ቁጥር | 2 | 1 | 1 | 100 | 2 | 2 | 100 | |
| | | | | | በምርምር ቢሮ ደረጃ የምርምርና ስርጸት የስራ ግመገማ ማድረግ | ቁጥር | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 | |
| | ፕሮግራሞችን፣ የምርምር ውጤቶችን እና አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ | 3 | ፕሮግራሞችን፣ የምርምር ውጤቶችን እና አገልግሎቶችን ማስተዋወቅ | የተዋወቁ የምርምር ውጤቶች እና አገልግሎቶች | የምርምር ሥራዎች እና የምርምር ውጤቶችን የሚያስተዋውቁ በራሪ ጽሁፎችን፤ ፖስተሮችን ባነሮችን፤ መጽሄቶችን፤ ሚኒ ሚዲያዎችን እንዲሁም የሬዲዮና የቴሌቭዥን ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ማሰራጨት | የማስተዋወቂያ ፅሑፎች | 6 | 2 | 0 | | 6 | 11 | 275 | |
| የመማርና ዕድገት እይታ | ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትና ማዘመን | 7 | ፋሲሊቲዎችን ማስፋፋትና ማዘመን | የተስፋፋና የተቋቋመ ፋሲሊቲ | የደን ዘቦታ /አርቦራተም ማቋቋም፡፡ | ፐርሰንት | 50 | 50 | 50 | 50 | 50 | 50 | 100 | |

| | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | የምርምርና የቴክኖሎጅ ሽግግር ስራዎችን በተሳለጠ መልኩ ለማከናወን የሚያስችል አንድ ራሱን የቻለ የህንጻ ኮምፕሌክስ (ዘመናዊ የምርምር ላቦራቶሪ፤ የምርምር ቢሮዎች፤ የህትመትና የምርምር ጹህፍ ማደራጃ ቦታዎች፤ የመረጃ ቋት ክፍሎች፤የአውደ ጥናት አዳራሾች እና ሙዚየም ያካተተ) ግንባታ ለማከናወን በባለሙያዎች ማስጠናትና ዲዛይኑን ማሰራት እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መነጋገር | በፐርሰንት | 100 | 25 | 0 | 0 | 100 | 15 | 15 | ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፍቃድ እና በጀት እስኪገኝ እየተጠበቀ ነው፡፡ ሕንጻው የሚይዘው ዝርዝር ተዘገዘጅቶአል፡፡ |
| | | | | | በሂርና የምርምር ጣቢያ የጥበቃ ቤት መስራት | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | በሂደት ላይ ነው፡፡ |
| | | | | | በሂርና የምርምር ጣቢያ የእቃ ማስቀመጫ ግምጃቤት መስራት | ቁጥር | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 0 | በሂደት ላይ ነው፡፡ |
| | | | | | በራሬ እና በባቢሌ ምርምር ጣቢያ ለዘር ማስቀመጫ የሚሆኑ መደርደርያዎች ማሰራት | ቁጥር | 10 | 0 | 0 | | 10 | 20 | 200 | ምቹ ሁኔታ ስለተፈጠረ |
| | | | | | በራሬ የምርምር ጣቢያ ለጠብታ መስኖ አጥር መስራት | በመቶኛ | 100 | 50 | 0 | 0 | 100 | 0 | 0 | ቅድመ ዝግጅት ስራ እየተሰራ ነው |
| | | | | | በባቢሌ የምርምር ጣቢያ የጥበቃ ቤት መስራት፡፡ | ብዛት | 1 | 1 | 1 | 100 | 1 | 1 | 100 | |
| | | | | | ከተለያዩ ቦታዎች ለምርምርና ስርጸት ስራዎቸ ተገዝተው ለሚመጡ ፍየሎችና በጎች ማቆያ ቤት(quarantine)መስራት | ብዛት | 2 | 0 | 0 | 0 | 2 | 0 | 0 | የቦታ ዝግ ጅት ስራ እየተሰራ ነው |
| | የአመራርንና የስራ | 11 | የአመራር የስራ ብቃትን፣ | የተሻሻለ የሰራተኞች እና | ለመምህራን የምርምር የንድፈ ሃሣብ አዘገጃጀት ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ቁጥር | 100 | 0 | 0 | 0 | 100 | 40 | 40 | |

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብቃትን፣ የፆታ ተሳትፎን፣ ፍትሃዊነትን፣ እና ተነሳሽነትን ማሳደግ | | ፍትሃዊነትን፣ እና ተነሳሽነትን ማሳደግ እና ፆታን ያማከለ አሰራር ማስፈን | ተቋማዊ አፈፃፀም | የመረጃ አያያዝና ትንተና ስልቶች ላይ ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ቁጥር | 150 | - | - | 120 | 150 | 90 | 60 | |
| | | | | | የሳይንሳዊ መጣጥፍ (Paper) አዘገጃጀትና የውጤት አቀራረብ ላይ ስልጠና መስጠት | የሰልጣኝ ቁጥር | 60 | 0 | 0 | 0 | 60 | 0 | 0 | በፕሮግራሞች መደራረብ ምክንያት |
| | | | | | ለምርምር የቴክኒክና የመስክ ረዳቶች በመረጃ አያያዝና አጠናቀር አጫጭር ስልጠናዎችን መስጠት | ብዛት | 75 | - | - | - | 75 | 60 | 80 | |
| | | | | | በምርምርና ስርጸት ስር በሚደረጉ የስልጠናና የአቅም ግንባታ ስራዎች የሴቶችን ተሳትፎ ማጎልበት | ከተሳታፊ በመቶኛ | 5 | - | - | - | 5 | 5 | 100 | |
| | በመልካም ተመክሮዎች ዙሪያ የልምድ ልውውጥ ማድረግና የስራ ፈጠራ ክህሎትና አስተሳሰብን ማሳደግ | 7 | በመልካም ተመክሮዎች ዙሪያ የልምድ ልውውጥ ማድረግና የስራ ፈጠራ ክህሎትና አስተሳሰብን ማሳደግ | ያደገ የስራ ፈጠራ ክህሎትና አስተሳሰብ፤ የተተገበረ መልካም ተሞክሮ | የዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎች/መምህራን በሃገር ውስት የሙያ ማህበራትና ሌሎች ኮንፈረንሶች ላይ እንዲሳተፉና የምርምር ግኝታቸውን እንዲያቀርቡ እገዛ ማድረግ | ቁጥር | 60 | 15 | 20 | 133 | 60 | 71 | 118.3 | |
| | | | | | ተመራማሪዎችና ሌሎች የምርምር ሰራቶኞች በሐገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የምርምር ማእከላትን እና ዩኒቨርሲቲዎችን ጎብኝተው የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማስቻል | ቁጥር | 10 | 4 | 4 | 100 | 10 | 13 | 130 | |